# የቆሪጥ ኑዛዜ

፩

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)

ነሐሴ ሁለት ሺ ሁለት ዓ.ም.

ሰው እንደ ማህበራዊ እንሰሳነቱ አረመኔ ድርጊቶችን ከመፈጸም እምነትና ህሊና፤ ከዚያ ዝቅ ያለውን ደግሞ ደመ-ነፍሳዊ ባህሪና ሕግ ለጉመው ይይዙታል። ዳሩ ግን የሰው ልጅ እነዚህን ሁሉ ማሰሪያዎች እንደ አልተገራች በቅሎ ቦጫጭቆ ሁሉን እየረገጠ ሲፈተለክ ምን ስቦ ይመልሰዋል? ሰብ እምነትን ክዶ፣ ህሊናውንና ደመነ-ፍሳዊ ባህሪውንም ከስብእናው ላይ በእንዶድ፣ በአመድ፣ በሞራ ሳሙናና በበረኪና ሙልጭ አርጎ አጥቦ ካስወገደ፤ በሰው ሰራሽ ሕግም ካልተገዛ፤ እንኳን ከመቅጠፍ፣ ከመካድና ከመዝረፍ የሰውን ገላ ቆራርርጦ ከጋለ ብረት ምጣድ ላይ እያስቀመጠ "ችስ..ስስ.. ጨር..ጨር"፣ እንደገና ገልበጥ እያደረገ "ችስ..ጨር..እስስስ ጨረ....ረረ" እያሰኘ ጠብሶ ከመብላት ከጠነጠነ ሐይል፣ አቅምን ከሚያኮሰመን ደዌና ከሞት ዉጭ ሌላ ምን የሚያግደው ነገር አለ?

አዎ በምርጫ ሳይሆን በተፈጥሮ ህሊና አልባ የሆነች በቅሎ ቅይዷን ፈታ፣ ልጓሟን ቦጭቃ ብትፈተለክም የማታ ማታ ደመ-ነፍሳዊ ባህሪዋ ከተራጋጪነት ወደ ሰላማዊ እንሰሳነት ይመልሳታል። ዳሩ ግን እምነትና ህሊናቸውን፣ደመ-ነፍሳዊ ባህሪያቸውንና ራሳቸው ያወጡትን "ሕግና ደንብ" ሳይቀር እንደ ቀበኛ ላም በጥርሳቸው ቦጫጭቀው የሚበሉ የአፍሪካ ገዥዎችንና አጫፋሪዎቻቸውን የግፍ ዶፍ ከማውረድ ምን ሸብቦ ይይዛቸዋል? በእነዚህ ከንቱዎች ምክንያት ድንግሉ የአፍሪካ ምድር የስንቱን ዜጎቹን ለጋ አካል ምጥምጥ አድርጎ በልቷል። የአፍሪካ ወንዞችስ የስንቱን ንጹሐን ዜጎች ደም እንደ ደለል ጎርሰዋል? ሕጻናት እንደ ቅጠል በርሃብና በበሽታ ቢለዋ በሚቀጠፉበት ዘመን ስንት የአውሮጳና የሰሜን አሜሪካ ባንኮች የአፍሪካን ንብረት ውጠው ቀርተዋል? ስንቱስ አፋቸውን እንደ ሰማይ ከፍተው በመዋጥ ላይ ይገኛሉ?

አለም እንደሚያውቀው እንደ አፍሪካ ባለስልጣናት ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ የሆነለት የአዳም ዘር ብዙ አይገኝም። በተደጋጋሚ እንደምናየው የአፍሪካ ገዥዎች እንኳን ሥር-የሰደደ በሽታ ሲደርስባቸው የሕዝብ ጉረሮ እየዘጉ የበሉት ሲያቅራቸው እንኳን እንደ ቤት አሽከር የሚያሽከረክሯቸውን የአየር መንገድ ሰራተኞች ያዝዙና በፈለጉበት ቦታ በረው ይታከማሉ። እነዚህ በዘመናዊ መንገድ አዋቅረናቸዋል፣ አሻሽለናቸዋል ወይም አሳድገናቸዋል እያሉ የሚዋሹላችው የጤና ተቋማት በስሙ እየለመኑ እርጥባን ለሚቀበሉበት የደቀቀና እንደ እንሰሳ ለሚያልቡት ሕዝብ እንጅ ለነሱ በቂ ወይም ምቹ የህክምና ቦታዎች ሆነው አያገኟቸውም። በዚህም መሰረት ጠቢያን አንዳንዴ የመረብ ኳስ፣ ሌላ ጊዜ የእግር ኳስ፣ ሲፈልጉም የከረቦላ ኳስ ወይም ጥንግ እያደረጉ ከሚጫወቱባት ቆሮ ባለስልጣናት መካከል አንዱ ታመመና ዶላሩን በአቆማዳ ጭኖ በአሜሪካን አገር ሚኒሶታ ግዛት ውስጥ ከሚገኘው ማዮ ክሊኒክ ለመታከም ሄደ። ባለስልጣኑ መታመሙ እንዳይታወቅ፤ እንደ ተራ ሰው ሆኖ እንዲታከም ተወሰነ። በእርጥባን የሚገኘው ገንዘብ በጉቦ መልክ እንደ አፈር ተዘርቶ ስሙና እድሜው እንደዚሁም መልኩ ምስጢር በሚጠብቁ ባለሙያዎች ተለዋወጠ። በተጨማሪም የሚታከምበት ቀን ክሊኒኩ ውስጥ አበሻ ሰራተኛም ሆነ በሽተኛ የማይገኝበት ቀን እንዲሆን ተመቻቼ።

ከማዮ ክሊኒኮች ወስጥ በአንደኛው የበሽተኛ መቀበያ አዳራሽ ውስጥ ያለች ጸሐፊ እንደማንኛውም በሽተኛ የሚሞላ ቅጽ ለዚህ "ተራ በሽተኛ" መስሎ ለሄደ ባለስልጣን ሰጠችው። በሽተኛው ባለስልጣንም የድሮ ስሙን ከጻፈ በኋላ ስም መቀየሩ ትዝ አለውና በፊት የጻፈውን ሰርዞ መልኩ ከተቀየረ በኋላ የተሰጠውን አዲስ ስም ከቅጹ ራስጌ ላይ ጻፈ። እድሜውንም በሁለት ደርዘኖች ያህል ቀንሶ አስቀመጠ። እድሜ ከሚለው ቀጥሎ ዘር(race) የሚለውን ቃል ሲያይ በቅቤ ያበደ ሽሮ እንደሸተተው አበሻ ምራቁ ጠብ አለና "የምናውቅብሽ ብሎ በልቡ ፎክሮ" ብሔር ወይም ብሐረሰቦች የሚል ምርጫ ፍለጋ አይኑ ተንከራተተ።። ዳሩ ግን ቅጹ በጥቅሉ ነጭ፣ ጥቁር፣ ላቲኖ፤ ኤሽያዊ ወይም ሌላ(other) የሚሉ ምርጫዎችን እንጅ እርሱ ደቁኖ የቀሰሰበትን 'ብሔር ወይም ብሔረሰቦች' የሚለውን ሐረግ ስላልያዘ  ግራ ገባው። ""where is the Nations and Nationalities section (ብሔር ብሔረሰቦች የሚለው ምርጫ የት አለ?) ብሎ ጸሐፊዋን ጠየቀ። "ይቅርታ ምን አልክ የኔ ጌታ?" ብላ በትህትና ጥያቄውን በጥያቄ መለሰች እርሷም ግራ ገባትና። "ዘር የሚለውን ክፍል በስክብሪቶ ጫፍ እየጠቆመ Nations and natio..." ብሎ ሳይጨርስ ቀለብ አደረገችና "ጌታዬ ከየትም አገር ብትመጣ እኛ ጉዳያችን አይደለም። ይህ አሜሪካ ነው። ዘር የሚለው እዚህ ቅጽ ላይ የገባው አንዳንድ በሽታዎች በዘር ስለሚተላለፉና ይህ ክሊኒክ ደግሞ በእንደነዚህ አይነት በሽታዎች ላይ ምርምር ስለሚያኪያሂድ ለዚያ ተብሎ ነው እንጅ ለሌላ ጉዳይ አይደለም። እንዲያውም እዚህ ጋ (በጣቷ እየጠቆመች) በጥቃቅን የተጻፈው 'ፈቃደኛ ከሆክ' ስለሚል ጥያቄውን መዝለልም ትችላለህ!" ብላ ካብራራች በኋላ "ለመሆኑ ኢንሹራንስ አለህ?" ስትል ጠየቀችው? "እኛ የገንዘብ ችግር የለብንም ማዮ ክሊኒክን እንዳለም ቢሆን መግዛት እንችላለን" አለ። ሴትዮዋም በልቧ "ታዲያ ሌላ ማዮ ክሊኒክ አገርህ መክፈት ሲገባህ እዚህ ምን አንከረፈፈህ?" አለች። "በነገራችን ላይ ቅድም ስለዘር ጉዳይ የጠየኩሽ በነገሩ አልስማማ ብዬ አይደለም። እንዲያውም ለእኛ ዋናውና ትልቁ የህይወት መርሀችን የሰውን ልጅ በዘር ከፋፍሎ መብቱን ማስጠበቅ ነው" አለ። ምን አጨቃጨቀኝ በሚል መንፈስ (ያለው እንደገባት ሁሉ) መልካም አለችና ተገላገለችው።

በሽተኛው “ከአሜሪካ እንዲህ አይነት ኋላቀር አሰራር አልጠበኩም ነበር። እኛ ስንቱን ጎሳ አብጠርጥረን በመልክ በመልኩ አስቀምጠን መብቱን ባስጠበቅንበት የሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን ጥቁር ቆዳ የለበሰውን ሁሉ አንድ ላይ ደብሎ ጥቁር ወይም ‘አፍሪካን አሜሪካን” እያሉ በማንነቱ እንዲያፍር ማድረግ ምን ይባላል? ኩኩዩ ጥቁር ኬንያ አሜሪካዊ፣ ኢቦ ጥቁር ናይጀሪያ አሜሪካዊ፣ አፋር ጥቁር ክልል-ሁለት የአፍሪካ ቀንድ አሜሪካዊ ወዘተርፈ እያሉ ማስቀመጥ ከባድ ነገር ሆኖ ነው? በስንት እደ-ጥበብ መጥቀናል፣ ለሰብአዊ መብት ተከራካሪ ከእኛ በላይ ለአሳር እያሉ የሚንበጣረሩት ‘የሕዝብና ሕዝቦችን፤ የብሔርና ብሔረሰቦችን’ መብት ሳያስከብሩ፤ ዘራቸውንም በመታወቂያና በፓስፖርታቸው ላይ ሳያስቀምጡ ነው? ወቼው ጉድ! ድንቄም የሰብአዊ መብት አክባሪ! አባይን ያላዬ ምንጭ ያመሰግናል!” እያለ ተገረመ። ቀጥሎም “ለነገሩ ይህንን ዘር ዝምብሎ አንድላይ በማጀልና ብሔር ብሔረሰቦችን በክልል ሳይሆን እንደ ነፍጠኞች አንድ ላይ ጨፍልቆ እንዲኖሩ በማስገደድ በኩልስ የዘመኑ ወዳጃችን ቻይናን የሚስተካከል የለም። ዳሩ እኛ ምን አገባን! ከቻይና ጋር ዋናው ቁርኝታችን “የኢንፎርሜሽን’ ጮራ ማስገቢያ ቀዳዳዎችን ሁሉ በቡትቶ ጥቅጥቅ አድርጎ እንዲደፍንልን ነው።” እያለ ብዙውን ጊዜ በሐሳቡ አንዳንዴም ድምጽ አውጥቶ እያጉረመረመ ‘ሌላ ዘር’ ከሚለው የዘር ምርጫ ሳጥን ላይ ምልክት አደረገና ፎርሙን ሞልቶ ጨርሶ አስረከበ። “ይህ ሰው እንደ እብድ ብቻውን ይናገራል ልበል ወይስ እየዘፈነ ነው” አለች ያላየች መስላ ስትከታተለው የነበረችው በሽተኛ አስተናጋጅ በልቧ።

“ዳያና ብራውን እባላለሁ የዶክተር ሽናይደር ረዳት ነኝ” ብላ ከመመርመሪያ ክፍሉ ውስጥ ይዛው ገባች። “እርሷ የብርቲሽ እርሱ ደግሞ የጀርመን ዘሮች” መሆን አለባቸው አለ ዘር የህይወቱ መርህ የሆነው በሽተኛ በሆዱ። “ዛሬ ምን እንድንረዳህ ትፈልጋለህ” ብላ ጠየቀችው። “ሐኪም ቤት መችም ሊበላ ሊጠጣ አይመጣም የጤና ችግር ሲኖር እንጅ” ብሎ ለመቀለድ ከጀለ። ሴትዮዋም በቀልዱ ተመስጣ ሳይሆን እንዲሁ በተለመደው የአሜሪካ ደንበኛን የማስተናገጃ ሳቅ፤ ጽገሬዳ አበባ በመሰለ ቀለም ክፈፍ ያበጀውን የላይኛውን ከንፈርዋን ወደ አፍንጫዋ ሰብሰብ አድርጋና ከላይ አራት ከታች ደግሞ ሁለት ያህል ጥርሶቿን አሳይታ “ እኮ የጤና ችግርህ ምንድን ነው ማለቴ ነው” ብላ ጠየቀች። ታካሚው ራሱን አከክ አከክ አደረገና “እንቅልፍ ማጣት አለ”። “ከመቼ ጀምሮ ስትል ጠየቀች። “እድሜየን በሙሉ ማለት ይቻላል! የባሰብኝ ግን ከዚህ ካለፈው ሚያዚያ ወር ጀምሮ ነው።” “ሚያዚያ ውስጥ ምን ተፈጠረ”? እርሱ ለሰው አይነገርም! (it is a private matter)” ብሎ ተቆጣ። “ይቅርታ መጠየቅ ስላለብኝ ነው! ለመሆኑ ምን ያህል ሰዓት ትተኛለህ?”። “እረ ምንም እንቅልፍ የለኝም በየደቂቃው ኩሽ ባለ ቁጥር ነው የምነቃው።” ዳያና በሽተኛውን ለዶክተሩ ከማስተላለፏ በፊት ማድረግ ያለባትን ነገር ከቅጹ ጋ እያየች “አለርጅ የሚሆኑብህ መድሃኒቶች ወይም ሌላ ነገር አለ?” ብላ ስትጠይቀው በፍጥነት “ተቀናቃኝና ነጻ ፕሬስ” ብሎ ሊመልስ ቃጣውና ቻይና ሳይሆን አሜሪካ ውስጥ እንዳለ ወዲያውኑ ተረድቶ “ሽብርተኛ” ብሎ መለሰ። “I Think we all are allergic to terrorists” አለችና ዳያና አሁን እንደ በፊቱ ስድስት ብቻ ሳይሆን በጥሩ የጥርስ ሐኪም ግራና ቀኝ የተተከሉትን ሁለት የወርቅ ጥርሶች ጨምሮ ሰላሳ ያህል ጥርሶቿን እያሳየች ከልቧ ተክ ተክ ብላ ሳቀች። “እውነት ለሽብርተኛ አለርጅክ ከሆንሽ ይህን ሰው ስትጨብጭ ምነው ከንፈርና ጉረሮሽ አላበጠ? ለምንስ አላስነጠሰሽና ትንፋሽ አላጠረሽ? ሰውነትሽንስ ለምን ሽፍታ አልወረረውና አላሳከከሽ?” አለ ድንገተኛ መንፈስ ክፍሉ ውስጥ ከተፍ ብሎ። በሽተኛውም “ከፕሬዘዳንቱ እስከ ተራው ዜጋ የአሜሪካን ሕዝብ ቀልብና ኩላሊት መጨበጫ ዘዴ ድሮስ መቼ አጣነው! ከልባቸውም ሆነ ከኪሳቸው ውስጥ ለመግባት ሳይታክቱ ስለሽብር ማውራት!!” አለና እርሱና ጓደኞቹ ለብዙ አመታት ባካበቱት የስራ ልምድ ተኩራርቶ ደረቱን ነፋ ትከሻውን ከፍ አድርጎ በኩራት ፈርጠም አለ። ቀጥላም “ታጨሳለህ” ብላ ስትጠይቀው ልቡ “ሰው ነው እማጨሰው!” ሲል ምላሱ ደግሞ “እንኳን ላጨስ ከሚያጨስ ሰው ጋር ለአንድ ሰከንድ ያህል መቆም እንኳን ይቀፈኛል” ሲል መለሰ።

ዳያና በረዳትነቷ የሚጠበቅባትን ያህል የጤንነት መረጃ ከሰበሰበች በኋላ የደም ግፊቱን፣ የልብ ትርታና ና የሙቀት መጠኑን ለመለካት ከላይ ያለውን ጃኬቱን እንዲያወልቅና ከመመርመሪያ አልጋው ላይ እንዲወጣ ጠይቃው ጃኬትቱን ሲያወልቅ የሲጃራ አገዳዎች እግር በራስ ሆነው ከጫት ቅጠሎች ጋር ከወለሉ ላይ ላይ ተራ በተራ ዱብ ዱብ አሉ። እንዲያውም ሁለቱ ሲጃራዎች ጫማዋ ውስጥ ገቡ። በትዝብት እንዳየችው ስላወቀ ከሚያጨስ ሰው ጋር ለአንድ ደቂቃም ቢሆን አብሮ መቆም ይቀፈኛል ያለው ፍጡር “ጓደኛዬ ያዝልኝ ብሎኝ ነው” አለና እንደተለመደው የበፊቱን ውሸት ለመሸፈን ሌላ ቅጥፈት አከለ። ዳያናም በውሸት ላይ ውሸት መቆለሉ ገባትና “እኔ እኮ ምንም አላልኩም። እዲህ አይነት ነገር ሲገጥመኝ ደግሞ የመጀመሪያ ጊዜዬ አይደለም! ብዙ አትጨነቅ! ምንም አይደለም! (that is ok)” እያለች የሚሰማው ሰው አይነት መስሏት ለማጽናናት ሞከረች። ቀጥላም “ሐኪሙ ሌላ በሽተኛ እያየ ስለሆነ እስከሚመጣ አስራምስት ደቂቃ ያህል ሊፈጅ ይችላልና በትእግስት ጠብቅ። እስከዚያው መጽሔት ማንበብ፣ ስልክ መደወል ወይም ሌላ ነገር መስራት ትችላለህ” ብላው ወጣች።

መመርመሪያ ክፍሉ ውስጥ የደም ግፊት፣ የጆሮና የአይን መመሪያዎች በራስጌ በኩል፤ ስለሰው አካልና ስለአንዳንድ በሽታዎች የሚያስረዱ ስእሎች ደግሞ ግራና ቀኝ ግርግዳው ላይ ተሰቅለዋል። በግራ የክፍሉ ማእዘን በኩል እንደዚሁ በቀይ ‘አደገኛ’ የሚል የተጻፈበት፤ የተጠቀሙበትን መርፌ፣ መቀስ፣ ምላጭ፣ ቢላዋና ሌላም ሌላም ስለት ነገሮች የሚከቱበት

ሳጥን ተሰቅሏል። በሽተኛው የተሰቀሉትን ስእሎች እየተመለከተ ሳይሆን በአይኑ እያዬ ወዲያ ወዲህ በመንጎራደድ ላይ ሳለ ከእጅ ስልኩ ላይ ከአዲስ አበባ ተደወለ። አንድ በእርሱ ስር የሚሰራ ካድሬ ቢጤ ነበር። "ሐሎ! … "አለ ካድሬው። ደዋዩ በደንብ አይሰማም ነበር። "አይሰማም ጮክ ብለህ ተናገር ሐሎ …ሐሎ… ሐሎ…" አለ በሽተኛው በአለቅነት መንፈስ። "ይኸ ራሱን እሳት ብሎ የሚጠራው የሽብርተኞች ቴሌቪዥን እንደገና ስራውን ጀመረ!!" አለ ካድሬው በሐዘን ተሞልቶ። "እሳት አባትህ ይጥፋና ታዲያ እሳት ሲቀጣጠል በፍጥነት የእሳት አደጋ ይጠራል እንጅ እኔ አሁን ሐኪም ቤት ውስጥ ሆኜ ምን አድርግ ነው የምትለኝ"

በሽተኛው ከወደቁበት ለቃቅሞ ካነሳቸው የኒያላ ሲጃራዎች ውስጥ አንዱን አፉ ውስጥ ከተተ። ከንፈሮቹን እንደ ምንጭር ሞጥሞጥ አድርጎና ወደ ቀኝ አጣሞ ማጨስ ክልክል ነው የሚለው ጽሑፍ ፊትለፊት ቆሞ ሲጃራውን ለኮሰና ጉንጮቹን ስርጉድ፤ ስርጉድ መልሶ ደግሞ እንደተንፋ ፊኛ ወደ ውጪ አበጥ፤ አበጥ እያደረገ በተከታታይ ማግ፤ ማግ አድርጎ ጭሱን እፉ…ፍፍፍ.. እያለ እንደ ባተሌ የአበሻ ወይዘሮ ኩሽና ወደ ላይ ወደ ጣራው እያከታተለ ለቀቀው። የሲጃራው ጭስ በመጠኑም ቢሆን ወጣ። እሳት የፈጠረው ረመጥ ግን አሁንም ሳንባውን እየጠበሰው ነው። ደዋዩ በተቆራረጠ ድምጽ "አለህ? እየሰማሃኝ ነው? "መሰማሚያህ ይደፈንና አዎ እየሰማሁህ ነው ቀጥል" "የእሳት አደጋ ላልከው ሐላፊነቱ የተሰጣቸው የእሳት አደጋ ሰራተኞች እነ ሚስተር 'ሊ' ና ሚስተር 'ዉ' ባህርዳር፣ እነ ሚስተር ሁዋንግ፣ሴቱንግና ያ ደሞ ማነው… ሚስተር ጋንግ ደግሞ አዋሳ የተቀሩት እንደዚሁ ድሬዳዋ ለሽርሽር ሄደዋል። "ሽርሽር!!! ሺ.ር ይበልህና ሁሉም አንዴ መሄድ እንደሌለባቸው፤ ምን ጊዜም ተረኛ ሰው መኖር እንዳለበት አልተስማማንም ነበር?" "እኛማ የውሃ ጎርፍ ለቀን እንደገና እንዳይያያዝ አድርገን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እሳቱን ያጠፋነው መስሎን ነበራ! "የሞትክ! እንደ አንተ አይነቱ ገለባ እስካለ ድረስ አንድ እሳት ሲጠፋ ሌላ እሳት ይነሳል!" ይህንን እንኳ የማታውቅ ከርሳም ነህ!" አለው አሁንም በሐይለ ቃል። "ወይ! ወይ! …የቅዱስ ገብርኤል ያለህ እንዲያው እንዲህ እየተባልህ የምትበላው እንጀራ (ደሞ እንጀራ አልኩት ሊጥም ሲበዛበት ነው) ቢቀርብህ አይሻልም? ደሞ እርሱ ስልጣን እንዳለው ሁሉ የምንትስ ድርጅት አባል ታልሆንሽ፣ መዋጮም ታላዋጣሽ የጽዳት ሰራተኛነት ስራሽን ታጫለሽ ይለኛል። ወገኛ ሆዳም" አሉ በልባቸው የጽዳት ሰራተኛዋ እማማ የሽአረግ ካድሬውን አለቃው ሲወርፈው ሰምተው።

ወይዘሮ የሽአረግ ቁመታቸው እንደ አረግ ተስቦ ተስቦ እዚያ ላይ የደረሰ አንቱ የተባሉ የ፷፩ አመት ወይዘሮ ናቸው። ባለቤታቸው መምህር ተሾመ ገለታ በዘር ተከፋፍሎ መተላለቅንና የሰብአዊ መብት ረገጣን በመቃወማቸው ያው እንደ አብዛኛው የአገሪቱ እስረኛ ሁሉ ወንጀል ቢሮ ውስጥ እንደ ቂጣ ተጠፍጥፎ ተጋግሮላቸው ይህ ፍርድ ቤት የሚባለው የቅጣት ቤትም አጽድቆት ታስረው፣ ወቅታዊ ህክምናም ተከልክለው በበሽታ ከአስራ ሁለት አመታት በፊት ሞተዋል። ወንዱ ልጃቸው ከዩንቨርሲቲ ተጠልፎ ተወስዶ እስካሁን ይኑር ይሙት አይታወቅም። ሴቷ ልጃቸው ደግሞ (የባለስልጣናትና የጥቅም ተጋሪዎቻቸው ልጆች እነ ወይዘሮ የሽአረግ ሲከፍሉት በኖሩት ግብርና በስማቸው በሚለመነው እርጥባን ወደ አሜሪካ፣ አውሮጳና ቻይና ለትምህርት ሲሄዱ) ወይዘሮ የሽአረግ መምህር ተሾመ ገለታን ሲያገቡ የገዙትን ጌጣጌጥ ሳይቀር በጉቦ መልክ ሰጥተው ወደ ቤይሩት ለግርድና ተላከች። እንደሌሎች ስደተኛ የጦቢያ ሴት ልጆች ሁሉ የእማማ የሽአረግ አንድ ሴት ልጅም የባሪያ አሳዳሪዎቿ የመንፈስ ቀውስ አድርሰውባት ከሶስት አመታት በፊት ከፎቅ ላይ ተከስካሳ ሞተች። እሰከሬኗን እንኳ ለማየት ያልታደሉት እማማ የሽአረግ እስካሁን የተዋበውን ፎቶግራፏን ከደረታቸው ላይ ለጥፈው ሳያለቅሱ ቀኑ ምሽቶ አይነጋም። ይህቺ የሰውም ሆነ የፊደል ዘር መገኛ የምትባለዋ ኢትዮጵያ፣ ይህቺ የአፍሪካ የነጻነት ምሳሌ የምትባለዋ ጦቢያ፣ ይህቺ የወዘሮ የሽአረግ አባትና አጎት የጣሊያንን ጉረሮ አንቀው የሞቱላት ጦቢያ፣ ይህቺ የሶስቱ ሃይማኖቶች መሰረት እየተባለ የሚነገርላት ኢትዮጵያ፣ ይህቺ መጽሐፍ ቅዱስ በምእራፉ አንስቶ የማይጠግባት የጊዮን እናት፣ ነቢዩ መሐመድ በቁራኑ ሆሜር ደግሞ በብእሩ የእውነትና የፍትህ አገር ሲሉ የመሰከሩላት አቢሲኒያ፤ ፍርደ ገምድልና ውለታ ቢስ ሆና እንደ እማማ የሽአረግ ያሉትን የጀግና ልጆች፣ ሚስቶችና እናቶች ዛሬ በመጠሪያቸው በሐዘን ውስጥ ዘፍቃ፣ በችጋርና በበሽታ ቀፍድዳ የጣረሞት ኑሮ ታስኖራቸዋለች።

የእማማ የሽአረግን በችጋር መጠበስ ያሳዘነው አንድ ጎረቤታቸው በዚህም በዚያም ብሎ የቤተሰባቸውን የጀግንነት ታሪክ ደብቆ የጽዳት ሰራተኝነት ስራ ፈልጎላቸው ከሳምንት ሶስት ቀን እየሰሩ በሌሎች ቀናት ደግሞ የእንጦጦን ዳገት እየወጡ የባህር ዛፍ ቅጠል እየለቀሙ በመሸጥ ይተዳደራሉ። ካድሬውና ህክምና ላይ ያለው ጌታው በስልክ ሲነጋገሩ እማማ የሽአረግ ወገባቸውን በኩታ አደግድገው፤ ራሳቸውን ደግሞ እስከጆሯቸው ድረስ በጥቁር ሻሽ ግጥም አድርገው፤ በዚያ ኾንጣፋ ቁመታቸው ጎንበስ ቀና እያሉ ካድሬው ካለበት ቀጥሎ ያለውን ክፍል ያጸዱ ነበር። ሁለቱ ክፍሎች የተለያዩት በመከታ እንጅ ከግድግዳ ስላልሆነ በዚያ ላይ ደግሞ ካድሬውና አለቃው እንደ መብረቅ እየጮሁ ስለሚናግሩ የሚባባሉትን ያዳምጡ ነበር፡

*ካድሬው አለቃውን "የእሳትን ነገር ለኛ ተወው። በቁጥጥራችን ስር እናደርገዋለን። ደሞ ብዙ አትረበሽ። ከዚህ በፊት ስንት የራዲዎ ጣቢያዎችን የከፈቱብን ወሬኞች እርስ በራሳቸው ተናክሰው የደረሱበት አልጠፋም? ይህም አዲስ ነገር አይሆንም! ደጋግመን እንዳየነው እሳትን ፈጠርን ያሉ ሰዎችም በአጭር ጊዜ ውስጥ እርስ በራሳቸው ፍም ይወራወሩና  ራሳቸውን በራሳቸው አቃጥለው ይጠፋሉ!!" እያለ አለቃውን ሲያጽናና ከዚህ በፊት የፈራረሱትን ለሕዝብ ቆመናል ይሉ የነበሩንትን ድርጅቶች፣ ራዲዎ ጣቢዎችና ጋዜጦች በአይነ-ህሊናው አስታውሶ እሳትም ያ ሁኔታ ሊገጥመው እንደሚችል ተማምኖ ካድሬው ኪ….ኪ…. ብሎ ሳቀ። "ወቼው ጉድ! ምን ነው የእንሽርት ውሃ ሆነህ በቀረህ ኖሮ! ሽር .. ይበልህና ከርሳም ስላለህ ይሆን የኮረኮሩህን ያህል የምትስቀው? ዳሩ ሰው እውነቱን ሲነግሩት የኮረኮሩትን ያህል ይስቃል!" አሉ እማማ የሽአረግ ።*

*ካድሬው አሁንም የበለጠ እንጀራውን ለማብሰል "ስንቱን ከፊታችን የቆመውን ጸረ-ሕዝብ ሁሉ ስኳር እያላስን፣ ሕግንና አፈ ሙዝን እየተጠቀምን ሲቻል ተመልሶ የእኛን ጉልበት እንዲስም ወይም ስለእኛ ቅዱስነት እንዲዘፍን እያደረግን ሳይቻል ደግሞ በፍጥነት ወደ አለም በቃኝ እንዲያም ሲል ወደ መቃብር ቤት የምንልክ አገልጋዮችህን በታማኝነታችን እንደማትጠራጠር ደግሞ አምናለሁ" ሲል የጭንቅ ቀን ደራሽነቱንና ታማኝነቱን እንደገና አደሰ። "ለመሆኑ ያቺ አሮጊት ጠራጊ አለመኖራን አረጋግጠሃል ይህንን ሁሉ ስትለፈልፍ?" ብሎ ጠየቀ በሽተኛው አለቃ። "የእኛን እንቆቅልሽ እንኳን ይህቺ የተንቆሸቆሸች አሮጊት (የሰው ክብር የሚባል ከነሱ መዝገበ ቃላት ውስጥ የለም) እኒህ ኢንጅነር፣ ፕሮፌሰር፣ ዶክተር፣ ፒ ኤጅ ቪ(ፒ ኤች ዲ ለማለት ፈልጎ ነው)፣ ማንጤስ ማንጤስ ነን የሚሉት እዚያ አሁን አለህበት አገር ያሉት ሳይቀር መፍታት አቅቷቸዋል!" አለ ኪ...ኪ ብሎ በፌዝ እየሳቀ። የማዮ ክሊኒኩ በሽተኛም "የነሱን ነገር ተወው። ዲግሪያቸውን ያንጠለጠሉት ከላይ ከጭንቅላታቸው ሳይሆን ከታች ከመቀመጫቸው ላይ ነው! ምላሳቸውን ክንድ ያህል እየለቀቁ እርስ በራሳቸው ሲወራረፉ ኖረው ተራብተራ ወደመቃብር ከመሄድ በስተቀር ተስማምተው አንድ የሚሰሩት ነገር የለም" አለ። "መቼም ከአንተ በላይ አዋቂ አይደለሁም። እኔ በበኩሌ ግን ዲግሪአቸውን ያንጠለጠሉት አፋቸውና መቀመጫቸው ላይ ነው ባይ ነኝ። እንዴት ማለት የሰው ልጅነት! የዲግሪውን ግማሽ ቀደድ እያደረጉ ያ ምንድነው ….በቅጠል ተከፍኖ በዳቦ መካከል የተቀበረ ስጋ አዎ… ሐምበርገር ሲበሉበት፤ የተቀረውን ደግሞ እንደ ሽንት ቤት ወረቀት እየቦጨቁ ከታች ሲጸዳዱበት ይኖሩና እንዳልከው ሲሞቱ ፕሮፌሰር ማንትስ፣ ዶክተር ማንትስ፣ ኢንጅነር ቀበጥርሶ አረፉ እየተባለ የህይወት ታሪካቸው የቀብራቸው ቀን ይነበባል፣ ጋዜጣ ላይ አሁን አሁን ደግሞ ኢንተርኔት ላይ ይለጠፋል አለና!" ኪ…ኪ… ብሎ የንቀት ሳቅ ሳቀ። "ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ ይሉሃል ይህቺ ናት! ጥሩ አድርገህ አስቀመጥከው አለ" ባለስልጣኑ በካድሬው አስተያዬት ተደስቶ።*

*"ስንቱን  ጸረ ሕዝብ …አፈ ሙዝ ተጠቅመን …በፍጥነት ወደ አለም በቃኝ እንዲያም ሲል ወደ መቃብር .." ብሎ ሲናገር ካድሬውን የሰሙ ሚስኪኗ እማ-ጠራጊዋ ከወዲያ ወዲህ ሲወራጭ የነበረውን መወልወያ ቆም አድርገውና ካድሬው እንዳያያቸው ጥግ ይዘው "አንቺ የጭንቅ አማላጅቱ፣ አንተ ፈጣሪ ክርስቶስ ሆይ! እውነት እኔ ማይሟ አሮጊት፤ እኔ በአውራ ጣቴ እምፈርመዋ ደንቆሮዋ እንኳን በዚህ ቢሮ፣ በዚች በጦቢያ ምድር ላይ የማየውን ቅጥፈት፣ ክህደት፣ በሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ተንኮል፣ ደባ፣ ግፍና ጭካኔ ማየት ተስኗችሁ ነው ዝም ያላችሁት" እንዳሉ የሞቱት ባለቤታቸው፣ ወጥተው ሳይመለሱ የቀሩት ልጆቻቸው፣በግፍ የተረሸኑት ጎረቢቶቻቸውና ባጠቃላይ የጦቢያ ሕዝብ መከራ ተደበላልቆ መጣባቸውና ካድሬው እንዳይሰማቸው የቀሚሳቸውን ጫፍ አፋቸው ውስጥ ጠቅጥቀው የእንባ ጎርፍና ማእበል በፊታቸው ላይ እመር፣ ኩፍስ፣ ከብለል እያለ እየፈሰሰ እርር ብለው አለቀሱ። እንደወትሮ ሁሉ ግድቡን ፈንቅሎ እንደሚያመልጥ ወንዝ በሚፈሰው እንባቸው ሐዘናቸው እየተገመደለ ሲቀንስላቸው ያንን ረጅም ክንዳቸውና እጃቸውን ወደ ጣራው ዘርግተው "አምላክ ሆይ! እግዚኦ መሀርነ …ክርስቶስ! ይህንን የተጎሳቆለ ሕዝብ ይቅር በለው! ጦቢያ እጆችዋን ወደ አንተ ዘርግታለችና ሰላም አውርድላት " ብለው ከንፈራቸውን ብቻ እያንቀሳቀሱ እግዚአብሔርን ተማጸኑ።*

*ባለስልጣኑ በሽተኛም ካድሬው "ራሳቸው በራሳቸው ፍም ተወራውረው ራሳቸውን በራሳቸው ያጠፋሉ" ከዚያ ቀጥሎም ታማኝነቱን ለማረጋገጥ "ስንቱን ከፊታችን የቆመውን እስር ቤትም ሆነ መቃብር ቤት የላክን ታማኞች" ያለውን ደጋግሞ እንደ ቆንጆ ሙዚቃ አዳመጠና እንደ ካድሬው ኪ..ኪ.. ብሎ ባይስቅም ሲጃራውን በጥርሶቹ እንደያዘ በደስታ ፈርጠም አለ። ወዲያው ትንሽ ሳይቆይ ደግሞ እሳት እስከሚጠፋ የሚያደርሰው ጉዳት ታየውና የተለመደው እብደቱ ድንገት አገረሸበት። "ስማ አንተ! እሳቶች እርስ በራሳቸው ዱላ እስከሚማዘዙ ተጎልተህ አትጠብቅ። ጭራሽ እንዲህ አይነት እድል አትስጡ። አሁኑኑ ሁሉንም የእሳት አደጋ ሰራተኞች ከእየሄዱበት ፈልጋችሁ አስቸኳይ እርምጃ ይወሰድ። እነሱ እስኪመጡ ቻይና ኢምባሲ ለ'ኢመርጀንሲ' ያስቀመጧቸው መሐንዲሶች ካሉ ጠይቁ"። ብሎ ባለስልጣኑ ሳይጨርስ "አዎ እንኳን እኛ እላይ እጫፍ ድረስ ያሉት ትላልቅ ባለስልጣኖች ሁሉ ሌላውን ስራቸውን ትተው እሳት ማጥፋቱ ላይ እየተረባረቡ ነው። እንኳን እዚህ ውጪ አገር ላሉት የቻይና ኢምባሲዎች ሁሉ እየደወልን ነው።" አለ ካድሬው አለቃው ባያየውም ከወገቡ ጎንበስ ብሎ በታዛዥነት መንፈስ። በሽተኛው "እዚህ አሜሪካ ላለው ግን አትደውሉ እኔ አሁኑኑ እደውላለሁ" አለና ስልኩን በሐይል ጥርቅም አደረገው።*

ከማስተወሻው ላይ "የድንገተኛ አደጋ የስልክ ቁጥሮች" ከሚለው ርእስ ውስጥ ፴፭ የቻይና ቁጥሮች በቀይ ቀለም ተደርድረዋል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በአሜሪካ የቻይናን ኢምባሲ ቁጥር ነበር።` ደመነፍሳዊ ባህሪው እዝለ-ልቡናውን ተቆጣጥሮት እየተርበተበተ "ሐሎ…ሐሎ ቻይና ኢምባሲ?" "አዎ ምን ልርዳዎት የኔ ጌታ ….!" "አምባሳደሩን በአስቸኳይ ማነጋገር እፈልጋለሁ!" "ይቅርታ ማነህ ለመሆኑ ….." ስትል ጠየቀች ስልኩን ያነሳቸው። የጠየቀችውን አላዳመጠም። "ምስራቅ አፍሪካ በሚገኙት የቻይና ዜጎች ላይ ያነጣጠረ ኢሳት የሚባል ነውጠኛ የዜና አውታር አደገኛ ሁኔታ እየፈጠረ ነው …." ብሎ እንደጨረሰ ምስራቅ አፍሪካ ከሚለው በስተቀር ሌላው ስላልገባት " "ጌታዬ ይህ ኢምባሲ ያለው አሜሪካ እንጅ ምስራቅ አፍሪካ ውስጥ አይደለም ….." በሽተኛው የባሰውን በሸቀ! ናላውም ዞረ! እንግሊዘኛ የማትችል ሰው እንዴት እዚህ ያስቀምጣሉ! እሳት ይገባሻል ….Fire! ነውጠኛ ይገባሻል! (You understand!) terrorist ሲል ጮኸ። በዚህ ወቅት ዲያና ከሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ሌላ በሽተኛ አስቀምጣ በመውጣት ላይ ሳለች ሰውየው እንደ እብድ ሲጮህ አዳመጠችው። "በፊትም አውቄዋለሁ ይህ ሰው የመንፈስ ጭንቀት አለበት። I think he is hearing voices! he keeps saying fire, terrorist bla.. la…" አለች። ቻይናዋ የስልክ አስተናጋጅ fire, terrorist የሚሉትን ቃላት እንደሰማች "ይህ ከሆነ ችግርህ እሳት አደጋና FBIን ጥራ እንጅ እኛ ምን ቤት ነን" እብድ (crazy) ብላ ስልኩን በሐይል ድርግም አደረገችው። ሳንባው ላይ የነበረው ረመጥ ተቀጣጥሎ የእሳቱ ምላስ አንገቱን ተሻግሮ ጭንቅላቱ ላይ ቦግ ቦግ አለበትና በእግሩም በእጁም ክፍሉ ውስጥ ያለውን እቃ ሁሉ ማተራመስና መስበር ጀመረ። ዲያና እርዳታ ለመጠየቅ ወደ ዋናው ቢሮ ሄደች።

ሕዝብ በአሰተሳሰብ፣ በሳይንስም ሆነ፣ በምጣኔ ሐብት ማደግ የሚችለው ሰው በነጻ አእምሮ ሲያስብ፣ እንደፈለገው መስማት፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ሲችል፣ ሐሳብ ያለምንም ገደብ መንሸራሸር ሲችል፣ እውቀት ጎጥ ድንበርና አጥር ሳያግደው እንደልቡ ሶስት መቶ ስልሳ ዲግሪ መሽከርከር ሲችል ነው" ብለው የሚያምኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ኢሳት የሚባል ነጻ የሕዝብ መገናኛ አገልግሎት መስርተዋል። ታዲያ ይህንና ሌሎችንም የሐሳብ መለዋዋጫ መንገዶች ለጦቢያ ሕዝብ እንዳይደርሱ የማዮ ክሊኒኩ በሽተኛ ባለስልጣንና ጓደኞቹ እንደዚሁም በዳረጎት የያዟቸው ካድሬዎቻቸው የፈለጉትን ያህል ገንዘብ፣ እንደ ወርቅ፣ መዳብና ሌሎችም ጥሬ እቃዎች፣ መሬትና የልጃገረድ መቅቡጥ ሳይቀር ለቻይናውያን እየሰጡ ያፍኑታል። ኢሳትና ሌሎች የዜና አውታሮችም ተስፋ ሳይቆርጡ መውደቅ መነሳቱን ቀጥለዋል።

አንዳንድ ተመራማሪዎች ሰው እውነቱን የሚናገረው እንደ ብስጭትና ፍርሃት ያሉ ደመነፍሳዊ ባህሪዎች ሰውነቱን ሲቆጣጠሩት ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ሰው ሐቅን የሚያወጣው ከእነዚህ ደመ-ነፍሳዊ ባህሪዎችም ሆነ ሌላ ውጫዊ አስገዳጅ ሐይል ነጻ ሲሆን ነው ይላሉ። ለሁለቱም አይነት መላ ምቶች በቂ መረጃ ባይኖርም እዚህ በሽተኛ ላይ ግን የመጀመሪያው የሰራ ይመስላል። እንደማንኛውም በሐይል፣ በማጭበርብርና በማታለል ስልጣን ላይ እንደሚኖር አገዛዝ ሁሉ በሽተኛውና ጓደኞቹ የተበተቡት ሥርዓትም ነጻ የሕዝብ መገናኛ አገልግሎቶችን ከሲኦል በላይ ይፈራሉ። እነዚህ አገልግሎቶች የተደበቀን አሰቃቂ ወንጀል፣ እየተፈጸመ ያለን ግፍ፣ ወደፊት በአገር በሕዝብ ላይ ሊመጣ የሚችለውን መቅሰፍት ለአገርም ሆነ ለአለም ሕዝብ ያሳውቃሉ። አዎ እነዚህ አገልግሎቶች በደንብ ከተዋቀሩ፣ ተጠያቂነትንና ሥነ-ምግባርን ከተላበሱ ተራራ ላይ እየወጡ፣ ሸለቆ ውስጥ እየገቡ፣ ክልል እየሰበሩና ወንዝ እየተሻገሩ ሕዝብን በእውቀት ያስታጥቃሉ፣ መብቱን እንዲያውቅ ያደርጋሉ፣ ሕዝብን ከሕዝብም ያቀራርባሉ። ይህ በሽተኛም ሆነ ጓደኞቹ ይህን የነጻ መገናኛዎችን ሐይል ጠንቅቀው ያውቃሉ። ከሰማኒያ የሚቀናቀኑ ድርጅቶች፣ ከሰላሳ ብርጌዶች ጦር ይልቅ ነጻ የሕዝብ መገናኛ አገልግሎት ሲነሳ እንደ ባህር ቁጠማ ይንቀጠቀጣሉ። ዛር እንደያዘው ሰውም ያጎራሉ። የቤት አመል ገበያ ይወጣል እንደሚባለው የነጻ መገናኛ አገልግሎት ሲነሳ የሚያስጎራው፣ ወንበር በቡጢ የሚያስመታው፣ መስታወት የሚያሰብረውና የስራ በልደረቦቹንም መከራ የሚያስበላው ቆሪጥ ሚኒሶታም ተከትሎ መጥቶ እንደ እብድ አስጮኸው፣ የስራ ጓደኛውንም ሆነ የቻይና ኢምባሲን ሰራተኛ አስወረፈው። እንደ አለመታደል የሰው ደም ወይም ስቃይ ካላዬ የማይሰክነው ይህ ቆሪጥ በዚህ ወቅትም ከናላው ላይ ቁጢጥ ብሎ እንደዚህ ሲል ተናዘዘ።

"ቻይና ይህ ነበር ውላችን! ቻይና.. ቻይና…. ይህ ነበር ወይ ውላችን? እንኳን ከኪሳችን የነበረውን የለመነውን ገንዘብ ሁሉ ሳይቀር እጃችን እንዳነሳ ልንሰጥህ ስንዋዋል፤ የኢንፎርሜሽን ማፈኛ ጥበብ ከሰጠኸን ከማንኛውም አይነት ማእድን ተጠቃሚ እንደምትሆን ስንነግርህ ይህ ነበር ውላችን? ቻይና ይህ ነበር ወይ ውላችን? እኛ የማንፈልገውን የወሬ ምንጭ ሁሉ ዝጋ፣ ስልክና ፋክስ ጥለፍ ብለን ስንዋዋልህ ምን ነበር ስምምነታችን? ቻይና … እነ 'ሊ' … እነ 'ሁዋንግ'… አየሩን ለነውጠኛ ክፍት አድርገው ሺርሺር እንዲሄዱ ነበር ውላችን! ነበር ወይ ቻይና!! ነበር!! ቻይና ከእነሱዳን ተማር። አየህ! ሱዳን ትንሽ መሬት ቦጭቀን ስንሰጠው ሶስት ሺህ ኪሎሜትር ድንበር ከተቀናቃኝ ይጠብቅልናል። ጅቡቲ ወደቡን ስንጠቀምለት የምንፈልጋቸውን ሰዎች ሁሉ ማጅራታቸውን እያነቀ ይሰጠናል። ኬንያውያን የውሃ መብራት ሐይል ስናሳያቸው ሰላማችንን የሚያደፈሩስትን ሁሉ እስር ቤት ያጉሩልናል! በፈለግነው ጊዜም ከመሐል እጃችን ላይ ያስቀምጡልናል! ተው ቻይና! ትንሽ ሰጥቶ ማግበስበስ ይቅርብሃ!" ግው! በውስጥ የተዘጋውን በር። "ኦ ሎርድ " አለች ከውጪ ሆና ታደምጥ የነበረች አንድ

የክሊኒኩ ሰራተኛ! ላጥ! የተሰቀለውን ምስል!! "እሳት! ካድሬው እንዳለው ራስህ በራስህ መጥፋትህ አይቀርም! እኛ ግን ለዚያም ጊዜ አንሰጥህ! እሳት! ጠብቅ አመድ ትሆናለህ! ጠብቅ ጎርፍ እንለቅብሃለን!!" እያለ ሲወራጭ ያንን መርፌና ቢለዋ ይዞ የተሰቀለ ሳጥን በራስ ቅሉ ከግድግዳው ጋር 'ድው' ሲያደርገው ሳምንት ሙሉ ያጠራቀሙት ስለት የህክምና መሳሪያ በአካሉ ላይ ፍስስ አለ። የመርፌ መዓት በልብሱ ላይ ተከሰከሰና የተቆጣች ጃርት መስሎ ቁጭ አለ።

በሽተኛው እዚያ እንደ አምላክ የሚመለክበት፣ እዚያ ትንሹም ትልቁም ቀና ብሎ ሳያይ እሚሰግድለት፣ እዚያ ተንኮሉና ሸሩ ሁሉ ተጠንስሶ እሚደፈደፍበት፣ እዚያ ስንቱ ክቡር ዜጋ ሞት እሚፈረድበት፣ ስንቱ ደግሞ እንዲታሰር፣ ንብረቱን እንዲቀማ፣ እንዲጠለፍ፣ እንዲሰደድ ወዘተርፈ የሚበየንብት ቢሮው ውስጥ ያለ መስሎት እንደ ልማዱ ደነፋ፣ ግርግዳውን፣ ጠረጴዛውን በቡጢ በሩን በእግርጫ ደለዘው። የክሊኒኩ ሰራተኞች ተሰብስበው ዝቅ ባለ ድምጽ ይወያያሉ። መጀመሪያ ያየችው አስተናጋጅ " የባህል ወይም የቋንቋ ጉዳይ መስሎኝ ነው እንጅ ይህ በሽተኛ ቅጹን ሲሞላ ያልተለመዱ ነገሮችን ያደርግ ነበር። መጀመሪያ አንድ ስም ጻፈና ያንን ሰርዞ ሌላ ስም እንደገና ጻፈ። ስም መቼም በህይወትህ ልትረሳው የምትችለው የመጫረሻው ነገር ነው። ቀጥሎ ደግሞ ዘር ለምን ትጠይቂያለሽ ብሎ ተቆጣ። ለምን እንደሆነ አብራራሁለት። መልሶ ደግሞ ዘር መቁጠር መርሃችን ነው አለ። ቅጹን ሲሞላ ደግሞ ንግግር ይሁን ዘፈን ብቻ የማይገባኝ ድምጽ ያሰማ ነበር። መቼም የትውልድ ቀን ካርድ ሳያዩ መፍረድ አስቸጋሪ ነው እንጅ እድሜውንም በትክክል የተናገረ አይመስለኝም" አለች። "ጥሩ አድርገሽ ተመልክተሸዋል። እኔም አለርጅ የሚሆንብህ ነገር አለ ብዬ ስጠይቀው 'ሽብርተኛ' ብሎ ቁጭ! በ፳፰ አመታት የሙያ አገልግሎቴ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ አይነት መልስ ስሰማ። ከዚያ ደግም ታጨሳለህ ብዬ ስጠይቀው ከሚያጨስ ጋር ለሰከንድ መቆዬትም ያመኛል ያለው ሰውዬ ከመመርመሪያ አልጋው ላይ ሲወጣ ከኪሱ የተራገፈው ሲጋራ ወለሉን አለበሰው። ደግሞ አገራቸው ቅጠልን እንደ "ቲሹ" ይጠቀሙበት  እንደሆነም አላውቅም ቅጠልም ከሲጃራው ጋር ከኪሱ ዱብ ዱብ አለ።" አለች ዳያና

ገደል የመሳሰሉ ፖሊሶች በሩን በእርግጫ ሰብረው ሲገቡ በሽተኛው በጀርባው ተንጋሎ ሐኪም ለአነስተኛ ቀዶ ጥገና የተጠቀመት ቢላዋና መቀስ አንገቱ ላይ፣ የመርፌ መንጋ ደግሞ በለበሰው ልብስ ላይ ተከስክሶ አገኙት። "ራሱን ለመግደል ሙከራ ያደረገ ይመስላል" አለ ከፖሊሶቹ አንዱ።  የጤና ባለሙያዎቹ ግን ክፍሉ በሲጃራ ሽታ ተበክሎ፣ ልብሱ ከላይ እስከታች በላብ ተጠምቆ፣ አፉ በጣም የደረቀ ኩበት መስሎ፣ የልብ ትርታው 200 ደርሶ ከማግኘታቸው በስተቀር ብዙም ቶሎ ብሎ ለህይወቱ የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ አረጋገጡ። በሽተኛው ፖሊሶችን ሲያይ ያች ሰዓት እነ መምህሬ አደፍርስ 'በመጨረሻዋ ቀን ወዮልህ!' እያሉ የሚያስጠነቅቁባት የፍጻሜ ቀን መስላ ታየችው።  በእውነቱ በዚያች ሰዓት ሀኪም ቤት ሳይሆን "አዲስ አበባ" መንፈንቅለ መንግስት ተድርጎ እርሱም ሆነ ጓደኞቹም በየቢሯቸው እጃቸውን የሰጡ መሰለውና እንደ እንጨት ደርቆ ቀረ። እስከዚያች ሰዓት ድረስ ፖሊስና ወተዳርን የሚያየው እርሱ በማይፈልጋቸው ሰዎች ላይ አፈሙዛቸውን ሲደቅኑና ባሩድ እንደ ዶፍ ሲያወርዱ እንጅ እርሱን ሊይዙ ሲመጡ አልነበረም። በዚች ቀውጢ ሰዓት ተንኮል መስራት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ትዝ ብለውት የማያውቁት በልጅነቱ ይሰማቸው የነበሩት የጥፋት ውኃ፣ ሰዶምና ገሞራ፣ ሁሉ በአይነ ህሊናው መጡበት። "ለካ ሰው ምን ቢጥር፣ የፈለገውን ያህል ላለመውደቅ ቢፍጨረጨር የማታ ማታ መውደቁ አይቀርም!" እያለ ከልጅነት እስከ ውቀት የሰራውን የተንኮል፣ ክፋትና ወንጀል ክር ወደ ኋላ አጠንጥኖ ከናላው ቴፕ ውስጥ አስገብቶ ለራሱ ማዳመጥ ጀመረ። እርሱና ጓደኞቹ የተንኮል ድር እያደሩ የገደሉትና ያስገደሉትን ሕዝብ፣ እስርቤት አስገብተው የገረፉትና በመግረፍ ላይ ያሉትን ግፍ ተቀባይ፤ በርሃብ፣ በበሽታና በስደት የመከራ ቶፋ ውስጥ እየቀቀሉት ያለውን መከረኛ ሕዝብ፣ እርስ በርሱ ሲበላላ እንዲኖር ስለት ያዘጋጁለትን የወደፊት ትውልድ ሁሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በአእምሮው ውስጥ በትያትር መልክ ተመለከተው።

በእርግጥ "እድሜአችሁን ያርዝምልን፣ መልአክ ከስማይ ለእኛ ሲል ነው ያወረዳችሁ!" እያሉ እግራቸው ስር የሚወድቁትን የጥቅም ተካፋዮችን ድምፅም አዳመጠ። ነገር ግን ይህ የጥቅም ተካፋዮቹ ምስጋና በሰበብ አስባቡ በፈጠሩት ጦርነት፣ በቀሰቀሱት የጎሳ ግጭትና እንደ ግል ንብረቶቻቸው በሚያዝዟቸው ወታደሮቻቸው አማካኝነት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተቆለለውን የሬሳ ክምር፤ ከፊሉ  የራስ ቅሉ ተበረቃቅሶ፣ አንዳንዱ አንጀቱ ተጎልጉሎ ወጥቶ፣ የተቀረው እንደዚሁ እጁ፣ እግሩና ሌላ ሌላውም አካሉ ተቆራርጦ እየታየው የብዙሐኑን የሰቆቃ ለቅሶና የደም እንባ ሊሸፍንለት አልቻለም። እንዲያውም እርሱና ጓደኞቹ እንኳን ቆመው ሞተውም ወላጆቻቸውን የገደሉባቸው፣ ያሰሩባቸው፣ ያሰደዱባቸውና ለሌላ ለሌላም አሰቃቂ መከራ የዳረጉባቸው ልጆች፣ የልጅ ልጆችና የእነሱም ልጅና የልጅ ልጆች ባጠቃላይ መጭው ትውልዳቸው ሁሉ ለዘላለም ወላጆቻችንን፣ እያቶቻችንን፣ ቅደመ አያቶቻችንን፣ ምንጅላቶቻችንን ወዘተርፈ የገደሉብን፣ ያሰሩብን፣ ያሰቃዩብን፣ ያሰደዱብን እነሱ ናቸው እያሉ ሲያዝኑባቸውና ሲረግሟቸው ሰማቸው። ልጆቻቸውን የገደለባቸው ወላጆችም እንደዚሁ ነጠላቸውን ዘቅዝቀው፣ ጥቁር ለብሰውና ፊታቸውን ልጠው አንዴ መሬትን ሌላ ግዜ ፈጣሪን ወደ ላይ እያዩ፣ እንባቸውን እንደጎርፍ እያፈሰሱ "እግዚአብሔር ይይላችሁ" እያሉ ፍርዱን ከእግዚአብሔር ጋ በመጠበቅ ላይ እንዳሉ

ተመለከተ። በአጠቃላይ መጀመሪያ ተፈጥሮ የአለም ጭራ የሆነው አብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ "እንዲህ በሐዘን፣ በችጋርና በበሽታ እንደጠበሳችሁን እግዚአብሔር የስራችሁን ዋጋ ይክፈላችሁ!" እያለ ሲረግማቸው ተሰማው።

አዎ ለመጀመሪያ ጊዜ እንኳን ሌላው ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ሲያፍሩበት፤ ሕዝብም እንኳን  ከእነርሱ አብራክ የወጡትን፣ ወደ ፊት የሚወለዱትንም ልጅና የልጅልጆቻቸውን፣ የእነዚህንም ልጅና የልጅ ልጆች የዚያ የነፍሰ ገዳዩ፣ የሐሰተኛውና የግፈኛው ዘሮች እያለ ሲጠቋቆምባቸው ታየው። እርግጥ ነው! ዛሬ ለሆድና ለሌላም ሌላም ቁሳዊ ንብረቶች ሲሉ በአሽከርነት የሚያገለግሏቸው ከንቱዎች ሁሉ ቀን ሲከዳቸው ሕዝብ ገና ያላወቀውን የሚሰቀጥጥ ግፍ ሁሉ እየጎለጎሉ እንደሚያወጡት መንፈሱ አስታወሰው። በተመሳሳይ መንገድም ዛሬ ለጥቅማቸው ሲሉ የሚደግፏቸው የውጭ መንግስታትም ነገ መሬቱ ሲንሸራተትባቸው እንደ ሌሎች ወንጀለኛ አምባገነኖች ሁሉ ቀስታቸውን አዙረው በነፍሰ-ገዳይነት እንደሚወነጅሏቸው ታየው። ድፍን የጠቢያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ከዚያም አልፎ የአለም ሕዝብ እንደ ሂትለር፣ ስታሊንንና ኢድ አሚን በሕዝብ ጨፍጫፊነታቸው እርሱንም ሆነ የጥፋት ጓዶቹን እስከ አለም ፍጻሜ በታሪክ መዝግቧቸው እንደሚኖር ተገነዘበ። እንዲህ አይነቱ ለሰሚ ግራ የሆነ ነገር በዚያች አጭር ጊዜ ውስጥ ተመሰቃቅሎ እየመጣ ናላውን አዞረውና ይህ ሁሉ ስራችን የጋኒኑ የቆሪጥ ስራ እንጅ ስጋ የለበሰ ሰው የሚሰራው ስራ አይደለም ብሎ ራሱ በራሳቸው ላይ መሰከረ።

ዶ/ር ሽናይደር የቻለውን ያህል ስለበሽተኛው ታሪክ በዳያና በኩል ከተራዳና አገላብጦ ከመረመረ በኋላ "በሉ በደም ስር የሚገባ ፈሳሽ ቀጥሉና ሆስፒታል ውስጥ ይተኛ" የሚል ትእዛዝ አስተላለፈ። አእምሮው ሳይዘጋጅ በመጣበት ኑዛዜ የተረበሸው በሽተኛ ግን ወደ ሆስፒታል መሄድ አልፈልግም ብሎ መወራጨት ጀመረ። ነገር ግን 50-1-50 በሚባለው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አደገኛ የሆነ የአእምሮ በሽተኛን አስግድዶ ሆስፒታል ማስተኛት በሚያስችለው ሕግ መሰረት በፖሊስ ተገዶ እንዲተኛ ተደረገ። "ይህንን መወራጨቱን የሚያስታግስና የሚያስተኛ መድሃኒት ቶሎ ስጡት!" አለ አሁንም ዶክተሩ የመድሃኒቱን ስም፣ የሚሰጠውን መጠንና አሰጣጡን በግልጽ እያስረዳ። በሽተኛው ከተኛ በኋላ የተለያዩ የደምና የሽንት ምርመራዎች ተደረጉ። በአሜሪካን አገር የመንገድ ዳር መድሃኒት ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የሆነው አምፌታሚን በሽንቱ ውስጥ ከመታየቱ በስተቀር ሌላ ብዙም እንከን አልተገኘበትም። ለሙያዊ ምክር የተጠራው የአእምሮ የሐኪም በሽተኛውን ከመረመረና የሽንቱን ውጤት ከአዩ በኋላ "የመንገድ ዳር ተዳዳሪ ነው?" ሲል ጠየቀ። "እረ ማዮ ክሊኒክን መግዛት የሚችል የናጠጠ ሐብታም መሆኑን ተናግሯል!" ስትል መለሰች ነርሷ። "ይህ የሚያሳይሽ የሌለን ነገር እንዳለ ወይም እንደሚሆን አርጎ ማሰብ ወይም ማመን (delusion) ነው" አለ በእርግጥም በሽተኛው የናጠጠ ሐብታም መሆኑን ያልተረዳው የአእምሮ ሐኪም።

በደም ስሩ በኩል ፈሳሽና እብደትን የሚያቀዘቅዝ መድሐኒት ሰጥተውት ተኝቶ ሰመመን ላይ ሳለ በሽተኛው "እሳት ... እሳት አሁንም እሳት! ..." ይላል። ቆይቶ ደግሞ "ኢስት አፍሪካ!  ኢስት አፍሪካ ....እሳት ነደደ ይላል"። አሁንም  "እሳት...." ይልና ቀጥሎ ደግሞ "ኢስት አፍሪካ....!" ይላል። " ይህ በሽተኛ ደጋግሞ ኢስት አፍሪካ ይላል! እዚህ ሆስፒታል ውስጥ የሚሰራ የኢስት አፍሪካ ሰው ታውቃላችሁ?" ስትል ጠየቀች የበሽተኛው ነርስ ወደ ሌሎች የስራ ባልደረቦቿ ፊቷን አዙራ። "ሽዲን(whatever his name is) ከሶማሊያ ነው!" አለች ሌላዋ ነርስ። ሽምሰዲን ተጠርቶ ሲመጣ በሽተኛው ኢስት አፍሪካ የሚንለውን ትቶ በደከመ ድምጽ  "እሳት....! እሳት!" ይል ነበር። "ይህ ሰው ከሶማሊያ ሳይሆን ከኢቶቢያ መሆን አለበት። ኢሳት በኢቶቢያ ቆንቋ ፋዬር (fire) ማለት ነው። እንደ ኢሳት ነደድኩ ነው የሚለው" አለ እንዲተረጉም የተጠራው ሽምሰዲን። "ውስጥ ጭንቅላቱን አቃጥሎት ካልሆነ በስተቀር ከውጪ የሙቀቱ መጠን ግን ደህና ነው" አለች ነርሷ። በሽተኛው በተሰጠው መድሐኒት ምክንያት በሰመመን ውስጥ ሲዋኝ፤ አይኑ ጣረ ሞተ እንደያዘው አንዴ ወደ መሬት ሌላ ጊዜ ወደ ሰማይ ሲገለባበጥ ሽምሰዲን አተኩሮ ተመለከተና የመጀመሪያውን ትርጉም እንዲህ ብሎ አሻሻለው። "ይህ በሽተኛ በምድር በኢሳት ሲቃጠል እንደኖረ ሲሞትም ገሀነብ-እሳት (hell) ሲለበልበው  እንደሚኖር ነው የሚናገረው!" "ኦ ... ምስኪን!" እያሉ የሽምሰዲንን ትርጉም ያዳመጡ ሁሉ ለበሽተኛው ሊጸልዩለት አይናቸውን ጨፍነው አንገታቸውን ወደ መሬት ደፉ። በሽተኛው ግን እውነት ነርሷ እንዳለችው አንጎሉን አቃጥሎት ይሁን ወይም ሽምሰዲን እንዳለው በምድር ያቃጠለው እሳት ሰማይ ቤትም እንደሚጠብቀው እያሰበ አለዚያም ኢሳት የተባለው የብዙሐን መገናኛ አገልግሎት አሳስቦት አይታወቅም አሁንም ነጩምና ጥቁሩ የአይኑ ክፍል ዛቢያ ላይ እንደተቀመጠ ሉል በሚያስፈራ ሁኔታ እየተሽከረከረ "እሳት!!    ....እ....ሳት!! እ..እ...እ..ሳት!"  ማለቱን ቀጠለ።